ጁን 2018 QuickNotes መልእክት ቁ. 1

**የትምህርት ቦርድ ለ2019 የበጀት ዓመት $2.60 ቢልዮን ዶላር የስራ ማስኬጃ በጀት አፅድቋል።**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ማክሰኞ (ጁን 12) ለ2019 የትምህርት ዓመት $2.60 ቢሊዮን ዶላር የሥራ ማስኬጃ ባጀት በሙሉ ድምጽ አጽድቋል። በጀቱ ከዘንድሮው የበጀት ዓመት የ$77.2 ሚሊዮን ዶላር ጭማሪ /እድገት አሳይቷል። ይህም በዲስትሪክቱ ያለውን እድገት ለማስተዳደር እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ከፍተኛ ስኬት እንዲያገኙ በጣም አስፈላጊ በሆኑ ወሳኝነት ባላቸው ነገሮች ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ያስችላል።

ከ$77.2 ሚሊዮን ዶላር የሥራ ማስኬጃ በጀት ጭማሪ አብዛኛው ገንዘብ ቁጥራቸው እያደገ ለመጣው የተማሪዎች ቁጥር አገልግሎቶችን ለመጠበቅ፤የሥራ ጥራት/ቅልጥፍና/ ለማረጋገጥ እና ቅድሚያ ትኩረት ለሚሰጣቸው ስልታዊ ነገሮች ይውላል።

$17.1 ሚሊዮን በጀት የተገመተዉን አዳዲስ የሚገቡ 1,882 ተጨማሪ ተማሪዎችን እድገት ለመርዳት የ201.96 ተጨማሪ መምህራን እና የሠራተኛ መደቦችን ይጨምራል። በተጨማሪም፣ የበጀት ጭማሪዉ አካል በማድረግ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሴፕቴምበር ላይ የሚከፈተውን ቤያርድ ረስቲን አንደኛ ደረጃ ት/ቤትን (Bayard Rustin Elementary School) ጨምሮ፣ በተጨማሪ ቦታዎች ማስፋፋት ያደርጋል ።

በጀቱ ፕሮግራሞችን እና ቁልፍ የሆኑ የሥራ አካባቢዎችን ለማስፋፋት፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፣ $16.1 ሚሊዮን እና 20.4 መደቦችን አካቷል፦

- አዳዲስ የሥራ ዝግጁነት ሙያዎችን/አቅጣጫዎችን ማስተዋወቅ፣ አቪዬሽን እና ኤሮስፔስን ጨምሮ ስለ ሳይበርሰኪዩሪቲ፣ የእሳት አደጋ መከላከልና ደህንነት፣ ህግ አስከባሪነት እና አመራር
- ሁለትዮሽ-ቋንቋ/two-way elementary language immersion የኤለመንተሪ ቋንቋ ኢመርዥን ፕሮግራሞችን ይበልጥ መጨመር

- በኮምፒውተር ሳይንስ፣ ኮዲንግ እና ሮቦቲክስ ፕሮግራሞችን ማስፋፋት
- ከጁላይ 2019 ጀምሮ በሁለት ኤለመንተሪ ት/ቤቶች የተራዘመ-ዓመት ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ማድረግ
- የተሐድሶ ትምህርት ፕሮግራም ማስጀመር
- የኮሌጅ መግቢያ መስመሮችን እና የላቀ የኮሌጅ ጥራትና ስኬት ፕሮግራሞችን (ACES) ማስፋፋት
- የመካከለኛ እና ቀዳሚ የኮሌጅ ፕሮግራሞችን ማስፋፋት

[ስለ ስራ ማስኬጃ ባጀቱ የበለጠ ይወቁ]

**በሰመር ወቅት ተማሪዎች ነፃ ምግብ ይሰጣቸዋል።**

በርካታ የሰመር ት/ቤት ወይም የመዝናኛ ፕሮግራሞች የሚገኙ ተማሪዎች ከ Montgomery County የሰመር ምግብ ፕሮግራም ምግቦችን ያገኛሉ። ፕሮግራሙ በአነስተኛ-ገቢ የሚገኙ ተማሪዎች የት/ቤት ቁርሶችና ምሳዎች በማያገኙበት በሰመር ወራት አልሚነት ያላቸው ምግቦች ማግኘት መቻላቸውን ያረጋግጣል።

በካውንቲው ውስጥ ከጁን 18 ጀምሮ በሣምንቱ የሥራ ቀናት ነፃ ምግብ የሚሰጥባቸው ቦታዎች በግምት 120 ጣቢያዎች ሲሆኑ (በየጣቢያው የሚጀመርባቸው ቀኖች ይለያያል)። 18 አመት እድሜ እና ከዚያ በታች የሆኑ ልጆች፣ አካላዊና አእምሮአዊ ስንክልና ላላቸው ግለሰቦች እስከ 21 አመት እድሜ ምግብ የማግኘት ብቃት አላቸው።

በጠቅላላ ካውንቲው ውስጥ በበርካታ ቦታዎች ዕድሜያቸዉ 18 ወይም ከዚያ በታች ለሆኑ ቀጠሮ ሳያስፈልግ /በ walk-in ለሚመጡ ልጆች በየቀኑ ምሳ ይሰጣል። ስለ ቦታዎችና የምግብ ሰአቶች የተለየ መረጃ ለማግኘት:- [እዚህ ጠቅ ያድርጉ]።

ለተጨማሪ መረጃ፣ የምግብና የአመጋገብ አገልግሎቶች ክፍል/Division of Food and Nutrition Services በስልክ ቁጥር:- 301-284-4900 ይደውሉ።

**ለ2018-2019 የትምህርት አመት ተፈላጊ ክትባቶች**

በ2018–2019 ወደ ሰባተኛ ክፍል የሚገቡ ልጆች በሙሉ የ ቴታነስ - Tetanus-diphtheria-acellular pertussis (Tdap) እና መነጃይትስ - Meningococcal meningitis (MCV4) ክትባቶችን የትምህርት ዓመት ከመጀመሩ በፊት መውሰድ አለባቸው። በተጨማሪ፣ ከ8ኛ እስከ 11ኛ ክፍል ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አዲስ የሚገቡ ተማሪዎች በሙሉ Tdap እና MCV4 ክትባት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። ተማሪዎች የ Tdap እና MCV4 ክትባት ማስረጃ እንዲያቀርቡ ይጠበቃል። ልጆቻቸው ተገቢውን ክትባቶች በሙሉ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ

ወላጆች ሃኪም ዶክተሮቻቸውን በማነጋገር የህክምና ማስረጃዎችን ቅጂ ለልጆቻቸው ት/ቤት ነርስ በተቻለ ፍጥነት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል ነገር ግን ከማክሰኞ፣ ሴፕቴምበር 4 (የ2018–2019 የትምህርት ዓመት የመጀመሪያው ቀን) አስቀድሞ መሆን አለበት።

**ሰመር ለንባብ በጣም ጥሩ አመቺ ጊዜ ነው!**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ቤተመጻሕፍት/ላይብራሪዎች (MCPL) ከጁን 9 ጀምሮ እስከ ሴፕቴምበር 9 በሚካሄደው የዓመቱ የሰመር ንባብ ላይ እንዲሳተፉ ሁሉንም ተማሪዎች ይጋብዛሉ። የዚህ ዓመቱ አብይ ርዕስ "Libraries Rock." ነው። በሰመር ወቅት ለሚካሄዱት ብርቱ ጥረትን የሚጠይቁ/challenge በርካታ ሙዚቃዎች፣ አስደሳች ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች ይዘጋጁ።

በሰመር ወቅት በሙሉ መማርን ለማበረታታት፣ ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎችን፣ መጫወቻዎችን/games፣ የመጽሐፍት ዝርዝሮች፣ እና አስቂኝ የሆኑ ትምርት ነክ ዝግጅቶችን ፕሮግራሙ ያካትታል። እንቅስቃሴዎቹ በተጠናቀቁ ጊዜ ሽልማቶች (እስካላለቀ ድረስ) ይሰጣሉ። ተሳታፊዎች በፕሮግራሙ መመዝገብ የሚችሉ ሲሆን ያነበቡትን ወይም የተነበበላቸዉን መፃህፍት ዱካ መከታተል አላባቸዉ። ምዝገባ አውታረ መረብ ላይ እና በማንኛውም የMCPL ቅርንጫፍ ቤተመፃሕፍት ይቻላል።

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተመራቂዎችን ድምጽ ያዳምጡ (Hear the Voices of MCPS Grads)**

ከሜይ 29 እስከ ጁን 8 በተደረጉት የተማሪዎች መመረቂያ ሥነ-ሥርዓቶች ከ 11,000 በላይ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ዲፕሎማዎችን አግኝተዋል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የ2018 ክፍል አባላትን ታሪኮቻቸውን እና ፎተግራፎችን የሚያመለክት ቪድዮ በድረገጽ አዘጋጅቷል። ጥቂት ተመራቂዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስለነበራቸው ቆይታ እና የወደፊት እቅዶቻቸውን በሚመለከት ያካፈሉትን ሃሳብ ለማዳመጥ/ለመስማት ድረገጹን ይጎብኙ። ለ 2018 ተመራቂዎች "እንኳን ደስ አላችሁ!"

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተመራቂዎች ድምፅ